ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፥ በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም።

ምሳ ፳፪፥፮



# የተረካቢ ትውልድ አውደ ጥናት ዘገባ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የጽርሐ አርያም ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል

የተረካቢ ትውልድ አወደ ጥናት ኮሚቴ

Version 3.0

## ትኩረት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቀኖናዋን፣ ዶግማዋን እና ስርዕትዋን ጠብቃ በምዕራቡ አለም እንድትቀጥል የሚያስችል ተረካቢ ትውልድ በርእሰ አድባራት ጽርሐ አርያም ካቴድራል ማፍራት እንዴት እንችላለን?

June 28, 2022

parishcouncil@minnesotaselassie.org

በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኩሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሚቀጥለውን የእድገት እርምጃ ለመራመድ የሚያስችሏት ካህናት፣ ምዕመናን፣ እና ብዛት ያላቸው ተረካቢ ልጆች እግዚአብሔር ስላደላት፤ የጥናቱ አላማና ውጤትም ይህንን ለማስቻል እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ እንዳይውል ኮሚቴው አበክሮ ያሳስባል።

# Contents

1. መግቢያ ..... 2
2. መርህ ..... 4
3. ጥናቱ የተካሄደበት መንገድ ..... 5
4. ደረጃ ፩፦ ትኩረት (Identify the Problem Statement) ..... 6
5. ደረጃ ፪፦ ድምጽ መሰብሰብ (Collect voices) ..... 8
6. ደረጃ ፫፦ ትንታኔ (Analysis) ..... 9
7. ደረጃ ፬፦ መፍትሄ (Recommendation ) ..... 11
8. ማጠቃለያ ..... 22
9. አባሪ፦ የአውደ ጥናቱ አባላት ዝርዝር ..... 23
10. ተጨማሪ አባሪዎች (አባሪ 1-12 ) ..... 24

በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኩሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሚቀጥለውን የእድገት እርምጃ ለመራመድ የሚያስችሏት ካህናት፣ ምዕመናን፣ እና ብዛት ያላቸው ተረካቢ ልጆች እግዚአብሔር ስላደላት፤ የጥናቱ አላማና ውጤትም ይህንን ለማስቻል እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ እንዳይውል ኮሚቴው አበክሮ ያሳስባል።

# 1. መግቢያ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን።

**እግዚአብሔርን እረዳት አድርገን፤ ብዙዎች በለፉበት ጥሩ መሰረት ላይ ቆመን፤ የሚቀጥለውን እርምጃ እንራመዳለን።**

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የጽርሐ አርያም ቅድስት ሥላሴ ቤተ ካቴድራል ህጻናትን ተረካቢ ለማድረግ መጠነ ሰፊ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ።ካህናት አባቶች የቤተ እግዚአብሔርን ደጅ ከፍተው፣ ልጆችን ተቀብለው፣ አጥምቀው፣ ስመ ክርስትናን ሰጥተው፣ አቁርበው፣ ዘወትር ልጆችን እየባረኩና ቤተሰብ ለልጆች መልካም እንዲሆን እየመከሩ እና እያስተማሩ የልጆች ህይወት በመልካም ጎዳና እንዲሄድ ትልቅ አስተዋጽዎ ያደርጋሉ።ሰንበት ትምህርት ቤቱ እና ምዕመናኑ በፊት ከነበሩበት ቤተ ክርስቲያን ጀምሮ ልጆችን ኮትኩቶ ለማሳደግ በተለይ እሑድ ላይ የሀይማኖት ትምህርቶች ለልጆች እንዲሰጡ ያላሰለሰ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል። ካህናቱ እና ምዕመኑ በቅዱስ ሲኖዶስ ስር ለመሆን በወሰኑበት ጊዜ እና የራሳቸው ቋሚ ቤተ ክርስቲያን እስኪኖራቸው ድረስ ከአምስት ያላነሱ ቦታዎች ላይ በሚገለበሉበት ጊዜያት ሳይቀር በሚያገኙት ክፍሎች በመጠቀም ለልጆች ትምህርት እንዲሰጡ ማድረጉ ይታወሳል።

በተለይ ደግሞ ከ2016 እኤአ ጀምሮ ልጆች ከቤተ ክርስቲያናቸው ጋር የበለጠ ግንኙነት እንዲኖራቸው፣ ቅዳሴን፣ የቤተ ክርስቲያን ስርዓትን፣ ሃይማኖታዊ ትምህርቶችን፣ እና በቤተ ክርስቲያን የሚሰጡ አገልግሎቶችን ብሎም ባህላቸውን እና ሃገራቸውን በበለጠ መረዳት እንዲችሉ ለማድረግ የሚያስችላቸውን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በቤዛ ኩሉ ሰንበት ትምህርት ቤት አደራጅነት ዘወትር ቅዳሜ በሰፊው እንዲሰጥ መጀመሩ ተረካቢ ትውልድ ለማፍራት ከሚደረገው ጥረት መሃል የጎላ ድርሻን ይዞ እየሄደ ይገኛል። በዚህም የቅዳሜ የቋንቋ ትምህርት እስከ 380 ተማሪዎች በ10 ክፍሎች ውስጥ ተመዝግበው ከ25 ባላነሱ የበጎ ሥራ (volunteer) መምህራን በመረዳት ከፊደል ቆጠራ እስከ ስዋስው ጥናት ድረስ እየተማሩ ሲሆን፤ የሚሰጠው ትምህርት ልጆች በጣም ጥሩ የቋንቋ መሰረት እንዲኖራቸው እየረዳ ይገኛል። በተጨማሪም በሰንበት ትምህርት ቤቱ የሕጻናት ክፍል መሪነት፣ በስብከተ ወንጌል ክፍል ጥበቃ እና በበጎ ሥራ መምህራን ዘወትር እሑድ ከ3 እስከ 18 እድሜ ያሉ ልጆች ከቅዱስ ቁርባን በኋላ በሰባት ክፍሎች ውስጥ በእየ እድሜ ክልላቸው ሆነው የሃይማኖት ትምህርት ይሰጣቸዋል። የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፣ መዝሙርና ስርዓትን በዋናነት አድርጎ የሚሰጠው የእሑድ ትምህርት፤ በተጓዳኝ ልጆች ከእኩዮቻቸው ጋር ጥሩ ወንድማማችነተን እና እህትማማችነትን እንዲያዳብሩ እና ጠንካራ የማህበራዊ ግንኙነት ትስስር እንዲኖራቸው እየረዳ ይገኛል። እንዲሁም ልጆች በዘወትር ትምህርት ቤታቸው ከሚያጋጥማቸው በተለየ ቅዳሜና እሑዱ የሚሰጣቸው ትምህርት እነሱን በሚመስል የበጎ ሥራ መምህራን የሚቀርብ በመሆኑ ልጆች በእራሳቸው ላይ የበለጠ መተማመን እንዲኖራቸው የሚያደርግ እና ወደፊትም እነሱም ቤተ ክርስቲያናቸውን፣ ምዕመናንን፣ ብሎም ሃገርን ለሚጠቅሙ የበጎ አድራጎት ሥራዎችን ለመስራት እንዲያዘጋጁ በተግባር እንዲማሩ ይረዳቸዋል።

በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኩሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሚቀጥለውን የእድገት እርምጃ ለመራመድ የሚያስችሏት ካህናት፣ ምዕመናን፣ እና ብዛት ያላቸው ተረካቢ ልጆች እግዚአብሔር ስላደላት፤ የጥናቱ አላማና ውጤትም ይህንን ለማስቻል እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ እንዳይውል ኮሚቴው አበክሮ ያሳስባል።

ከዚህም ባሻገር ወላጆች እና የቤዛ ኲሉ ሰንበት ትምህርት ቤት በተለያየ ወቅት ልጆችን በማገናኘት ልጆች ጠንካራ ማኅበራዊ ትስስር እንዲኖራቸው ይደረጋሉ። በምሳሌነት በወላጆች አነሳሽነት ተቋቁመው የነበሩት የሴቶች ልጆች የቅድስት ማርያም እና የወንዶች ልጆች የቅዱስ ሚካኤል ማኅበራት ሊጠቀሱ ይችላሉ። በተጓዳኝ ልጆች እንደልጅነታቸው  እየተጫወቱ እንዲያጉ እና ከቤተ ክርስቲያን ወንደሞቻቸው እና እህቶቻቸው ጋር የማይረሱ ትዝታዎች እንዲኖራቸው በወላጆች እና በቤዛ ኲሉ ሰንበት ትምህርት ቤት የተለያዩ ዝግጅቶች (በተለይ በበጋ ወቅት) ይዘጋጁላቸዋል።

በአስተዳደር እና አወቃቀርም ቤተ ክርስቲያኒቱ ሕፃናት ተረካቢ እንዲሆኑ ለማድረግ ዋና አላማዋ እንደሆነ አስቀምጣለች። የቤተ ክርስቲያኑ መተዳደሪያ ደንብ ምዕራፍ ፪ አንቀጽ ፬ ቁጥር ፬ እንደሚያመለክተው የቤተ ክርስቲያኒቱ አንደኛው ተልዕኮ “ሕፃናትና ወጣቶች በሥነ ምግባር ታንጸው ሃይማኖትን በመጠበቅ አድገው አገርና ቤተ ክርስቲያንን ተረካቢ እንዲሆኑ ማስቻል ነው”። ይህንንም በመንተራስ የቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳደር ከ2015 እኤአ ጀምሮ ቀርጾ በአጠቃላይ ጉባኤው ያጸደቃቸውና አሁንም የሚሰራባቸው አራት ራዕዮች መሃከል አንዱ “ጠንካራ ተረካቢ ትውልድ ማፍራት” ነው። እነኝህ የአስተዳደር መሳሪያ በመሆን “ተረካቢ ትውልድ” የሚለው ዘወትር በቤተ ክርስቲያኑ አሰራር ውስጥ በዋናነት እንዲንጸባረቅ፣ ውይይት ላይ እንዲነሳ፣ ውሳኔዎች ላይ የበላይነት እንዲያገኝ እየረዱት መጥተዋል።

እንደሚታወቀው ቤተ ክርስቲያኒቱ ባዘረጋጀቻቸው መርሃ ግብሮች ልጆች እንዲሳተፉ ብሎም ከመርሃ ግብሮቹ የሚማሩትን ትምህርት ወደ ህይወታቸው እንዲተረጉሙ የማድረግ ኃላፊነቱን ይዞ ልጆች የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ተረካቢ እንዲሆኑ እጅግ በጣም ትልቁን የአንበሳ ድርሻ የሚወጣው ወላጅ እና ቤተሰብ ነው። በተለይ ወላጆች ለልጆች ፍቅርን በመስጠት፣ ምግባርን በማስተማር፣ ልጆች የሚማሩትን የቋንቋና የሃይማኖት ትምህርቶች ማጠናከሪያ በመስጠት እና በክርስቲያናዊ ህይወት ምሳሌ (role model) በመሆን ልጆችን መቅረጽ ብሎም የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ተረካቢ ለማድረግ ትልቅ አስተዋጽዎ ይጠበቅባቸዋል።

ከላይ በተጠቀሱት ጠንካራ መሰረቶች ላይ በመቆም የልጆችን ተረካቢነት በአንድ እርምጃ ወደፊት ለማሻገር እንዲረዳ የአጭር እና የረዥም ጊዜ እቅድ ማውጣት እንደሚገባ በመረዳት፤ በተለይ ከ 18 ዓመት እድሜ በላይ የሚሆኑት ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን ያላቸው ተሳትፎ ከሚጠበቀው በላይ አናሳ መሆኑን በመገንዘብ፤ የ2022-2024 የሚያገለግለው የሰበካ ጉባኤ በ December 2021 አወደ ጥናት እንዲደረግና የ5 ዓመት እቅድ ግብአት እንዲቀርብ ኮሚቴ አቋቁሟል። ይህ የአወደ ጥናት ኮሚቴ በቤተ ክርስቲያኑ ከልጆች ጋር ከሚገናኙ የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን መዋቅሮች የተውጣጡ ተወካዮች የተካተቱበት ነው፤ ለምሣሌ፦ ከማኅበረ ካህናት፣ ከሰበካ ጉባኤ፣ ከሰንበት ት/ቤት፣ ከወላጆች፣ ከመምህራን፣ እና ከወጣቶች በኮሚቴ ተካተዋል።

ከዚህ በመቀጠል ኮሚቴው አወደ ጥናቱን ለማካሄድ የተጠቀመባቸውን መርሆች፣ የሄደባቸውን መንገዶች፣ የደረሰባቸውን ግኝቶች እና በተረካቢ ትውልድ ዙሪያ የሚሰራውን ሥራ ወደሚቀጥለው ደረጃ ለማሻገር ያስፈልጋል ያላቸውን የአንድ ዓመት ሥራ እና የአምስት ዓመት ስልታዊ እቅድ በቅደም ተከተል ያቀርባል።

በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኲሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሚቀጥለውን የእድገት እርምጃ ለመራመድ የሚያስችሏት ካህናት፣ ምዕመናን፣ እና ብዛት ያላቸው ተረካቢ ልጆች እግዚአብሔር ስላደላት፤ የጥናቱ አላማና ውጤትም ይህንን ለማስቻል እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ እንዳይውል ኮሚቴው አበክሮ ያሳስባል።

## 2. መርህ

አወደ ጥናቱ ዋነኛ ትኩረት ያደረገው የአንድ ልጅ ክርስቲያናዊ ህይወትን በጽርሐ አርያም ቅድስት ሥላሴ ቤተ ካቴድራል ውስጥ በመልካም ሁኔታ ለመቅረጽ የሚያስችሉ የተሟሉ እና ሁለገብ ሁኔታዎችን መፍጠር እንዴት እንችላለን የሚለው ሃሳብ ላይ ሲሆን፤ ለዚህም አሰራር እንዲጠቅም ኮሚቴው የሚከተሉትን አምስት ዋና ዋና መርሆችን አውጥቷል

1. Common goal/outcome፦ ተመሳሳይ ግብ እንዳለን ማስመር [ልጆችን ማእከላዊ ያደረገ ውጤት]
2. Non-biased analysis፦ ሁሉንም አቅጣጫ የዳሰሰ፤ ወደ አንድ አቅጣጫ ያላዘነበለ ትንታኔ መስጠት
3. Synergized/aligned solution፦ ሊደጋገፉ የሚችሉ መፍትሔዎችን ማቅረብ
4. No one to blame፦ ጣት ለመጠቆም ሳይሆን የመሻሻያና የማደጊያ እድሎችን መፍጠር
5. Strengthening existing programs & adding/proposing new ፦ ያሉንን ጠንካራ መርሃ ግብሮች የበለጠ ማጠንከር፤ ባሉን ላይ ተጨማሪ መርሃ ግብሮች እንዲታከሉ ግብአት ማቅረብ

ለለውጥ አስተዳደር (change management) እንዲረዳ ለማስቻል እና ምክርና ሃሳብ ለመቀበል ኮሚቴው በተለያዩ ወቅቶች ከማኅበረ ካህናቱ፣ ከሰንበት ት/ቤት ስራ አመራር፣ ከመምህራን፣ እና ከሰበካ ጉባኤ አባላትጋር የደረሰባቸውን ሃሳቦች ከላይ የተጠቀሱትን አምስት መርሆች በመመርኮዝ ውይይት አካሂዷል። እንዲሁም May 8, 2022 በተደረገው የአጠቃላይ ጉባኤ ላይ ለተሳታፊዎቹ ኮሚቴው በወቅቱ የደረሰበንት አቅርቧል።

በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኩሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሚቀጥለውን የእድገት እርምጃ ለመራመድ የሚያስችሏት ካህናት፣ ምዕመናን፣ እና ብዛት ያላቸው ተረካቢ ልጆች እግዚአብሔር ስላደላት፤ የጥናቱ አላማና ውጤትም ይህንን ለማስቻል እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ እንዳይውል ኮሚቴው አበክሮ ያሳስባል።

# 3. ጥናቱ የተካሄደበት መንገድ

አወደ ጥናቱ በአራት ደረጃ ተከፍሎ ከ December 15, 2022 እስከ June 28, 2022 ድረስ ተካሂዷል። አራቱ ደረጃዎች በሚቀጥለው መግለጫ 1 ቀርበዋል።





*Figure 1 የአውደ ጥናቱ ሂደት*

ኮሚቴው እየአንድአንዱን ደረጃ ባለፈበት ወቅት የፈጸመውን ሥራ ለሰበካ ጉባኤው በቂ መረጃ እየሰጠና የተሰሩትን ስራዎች በመረጃ እያከማቸ ሥራውን ከአንድ ደረጃ ወደሚቀጥለው ደረጃ አሸጋግሯል። በአጠቃላይ ከDecember 15, 2022 ጀምሮ በአማካይ በሳምንት ሁለት ጊዜ በመሰብሰብ በተለይ እሑድ ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በኋላ እና አርብ ከ6 pm በኋላ በአብዛኛው በአካል እና አልፎ አልፎ በZoom በመገናኘት ሥራውን አገባዷል።

ከዚህ በመከተል ከደረጃ ፩ እስከ ደረጃ ፬ ያሉት የሥራ ውጤቶች ይቀርባሉ።

በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኲሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሚቀጥለውን የእድገት እርምጃ ለመራመድ የሚያስችሏት ካህናት፣ ምዕመናን፣ እና ብዛት ያላቸው ተረካቢ ልጆች እግዚአብሔር ስላደላት፤ የጥናቱ አላማና ውጤትም ይህንን ለማስቻል እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ እንዳይውል ኮሚቴው አበክሮ ያሳስባል።

## 4. ደረጃ ፩፡- ትኩረት (Identify the Problem Statement)

ኮሚቴው በመጀመሪያ ደረጃ መፍትሄ እንዲሰጥ የተጠየቀበት ዋና ጉዳይ ምንድን ነው የሚለውን አጥርቶ ለማወጣት በደረጃ ሥራው ላይ ዋና ትኩረት አድርጎ ተንቀሳቅሷል። በዚህም መሰረት በተለይ ዋናው ችግር ይታይበታል ከሚባለው የእድሜ ክልል በመነሳት ውይይቶችን በማድረግ፤ ከ18 በላይ የሚያስተምሩ መምህራን ጋር በመወያየት በማድረግ የሚከተሉት ዋና ዋና ነጥቦች ላይ ደርሷል፡-

a) ልጆችን ተረካቢ ለማድረግ በቅድሚያ ሃላፊነቱን ጠንቅቆ የተረዳ እና ለማስረከብ የሚረዳው መሳሪያ የታጠቀ አስረካቢ ትውልድ እንደሚያስፈልግ

b) ልጆች 18 አመት ሲሞላቸውና በራሳቸው ውሳኔን የመወሰን አቅም ሲያዳብሩ በግላቸው ወስነው ወደ ቤተ እግዚአብሔር እንዲመጡ ትልቅ ተጽእኖ ሊፈጥርባቸው የሚችለው ከ3 – 18 ዓመት ድረስ ውስጥ ያለፉበት የክርስትና ህይወት አስተዳደጋቸው ስለሆነ ከ3 – 18 በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት ሊዳሰስ እና ሊጠናከር እንደሚገባ

c) በመጨረሻም 18 ከሞላቸው በኋላ በተለይ የእንግሊዘኛ ቋንቋን ያማከለ የጉባኤ፣ የጸሎት፣ እና የውይይት መድረኮች ሊዘጋጁላቸል እንደሚያስፈልግ እና ከመገልገል ባለፈ ሃላፊነትን እየወሰዱ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማገልገል እንዲችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት እንደሚገባ ግንዛቤ ላይ ደርሷል።

ከላይ የተጠቀሱትን ሶስት ነጥቦች በመያዝ ኮሚቴው መፍትሄ ሊስጥ ይገባቸዋል ብሎ የቀረጸውና ለሚቀጥሉት ስራዎቹ መሪ ትልሙ ያደረገው የሚከተለውን ይሆናል፡-




*Figure 2 ትኩረት (Problem Statement)*

በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኩሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሚቀጥለውን የእድገት እርምጃ ለመራመድ የሚያስችሏት ካህናት፣ ምዕመናን፣ እና ብዛት ያላቸው ተረካቢ ልጆች እግዚአብሔር ስላደላት፤ የጥናቱ አላማና ውጤትም ይህንን ለማስቻል እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ እንዳይውል ኮሚቴው አበክሮ ያሳስባል።

ኮሚቴው ተደጋግሞ በቤተ ክርስቲያኑ የምንጠቀምበትን “ተረካቢ ትውልድ” የሚለውን ቃል በበለጠ መግለጽ አስፈላጊ መሆኑን አምኖበት ለዚህ ጥናት በሚከተለው መልኩ እንዲተረጎም አቅርቧል።

- “ምን ሲሆን ነው ተረካቢ ትወለድ አፍርተናል የምንለው” የሚለውን መለኪያ/ጥያቄ በመጠቀም
- *ተረካቢ ትውልድ ማለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቀኖናዋን፣ ዶግማዋን እና ስርዕትዋን ጠብቃ በምዕራቡ አለም እንድትቀጥል የሚያስችል ትውልድ ነው* በሚል አስቀምጦታል።

በዚህም መሰረት ጠንካራ ተረካቢ ትውልድ ለማፍራት፡-

a) ልጆችን ከስሩ በማዘጋጀት፣

b) ጎልማሳዎችን በቤተ ክርስቲያን እንዲሳተፉ እና እንዲያገለግሉ በማድረግ፣

c) እንዲሁም ወላጆችን የልጆች የቅርብ መምህር/ተከታታይ/ምሳሌ እንዲሆኑ በማስቻል ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ሚና ልትጫወት ትችላለች።

በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኲሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሚቀጥለውን የእድገት እርምጃ ለመራመድ የሚያስችሏት ካህናት፣ ምዕመናን፣ እና ብዛት ያላቸው ተረካቢ ልጆች እግዚአብሔር ስላደላት፤ የጥናቱ አላማና ውጤትም ይህንን ለማስቻል እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ እንዳይውል ኮሚቴው አበክሮ ያሳስባል።

## 5. ደረጃ ፫:- ድምጽ መሰብሰብ (Collect voices)

ለዚህ አወደ ጥናት እንዲረዳ ኮሚቴው የሚከተሉትን ድምጾች ሰብስቧል።

a) የሕፃናት እና ወጣቶች መጠይቅ (95 የተመለሰ ከ 6 ዓመት እስከ 23 ዓመት/በየክፍሉ እሑድ የታደለ) [አባሪ 1]

b) የአዋቂ ምዕመናን መጠይቅ (45 የተመልሰ፤ 36 online 9 በወረቀት) [አባሪ 2]

c) የሕፃናት ውይይት [አባሪ 3]

d) የወጣቶች ውይይት [አባሪ 4]

e) በፈቃድ የሚያስተምሩ መምህራን ጋር የተደረገ ውይይት

f) በሕፃናት ዙሪያ ብዙ ከሰሩ ካህናት ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ [አባሪ 5]

    a. ቀሲስ ሰይፈ

    b. አባ አትናቲዮስ

    c. ቀሲስ ዶ/ር ሶሎሞን

    d. ዲ/ን ጎርጎርዮስ

g) በተጨማሪም የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተመራቂዎች ለአቡነ ዘካሪያስ ስኮላርሰሺፕ ማመልከቻ ከጻፏቸው ጽሁፎች መሃከል ይህ ኮሚቴ ለተነሳበት ዓላማ ግባት ይሆናሉ ያላቸውን ጽሁፎች በጥናቱ ላይ አካቷል [አባሪ 6]።

እነኝህን ድምጾች ይዞ እየሰራ ያለውን ሥራ ለማካፈል እና ተጨማሪ ድምጽ ለመሰብሰብ እና ምክር ለማግኘት ኮሚቴው ከሚከተሉት የቤተ ክርስቲያኑ አካላት ጋር ተወያይቷል።

a) የደብሩ ካህናት

b) ሰበካ ጉባኤ

c) የሰንበት ት/ቤት አመራር

በአጠቃላይ ሲታይ የቤተ ክርስቲያኑ አካላት ያለውን ክፍተት ባጤነ መልኩ ወደሚቀጥለው የእድገት ደረጃ መሄድ አስፈላጊ መሆኑን ቢያምኑበትም እንዴት እንፍታው በሚለው ዙሪያ የተለያዩ አቀራረቦች ተስተውለዋል። ኮሚቴው የሃሳብ ልዩነቶችን እያመዛዘነ፣ የልጆችን ድምጽ የበለጠ ቦታ በመስጠት፣ አሰራሩን በምዕራፍ ሁለት ላይ በቀረቡት መርሆች በመመርኮዝ እና ዘላቂ ይሆናሉ ብሎ ወዳመናቸው የመፍትሄ ሃሳቦች ለመድረስ እንዲያስችለው በሚቀጥለው ምዕራፍ ይቀረበውን ትንታኔዎች አድርጓል።

በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኲሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሚቀጥለውን የእድገት እርምጃ ለመራመድ የሚያስችሏት ካህናት፣ ምዕመናን፣ እና ብዛት ያላቸው ተረካቢ ልጆች እግዚአብሔር ስላደላት፤ የጥናቱ አላማና ውጤትም ይህንን ለማስቻል እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ እንዳይውል ኮሚቴው አበክሮ ያሳስባል።

## 6. ደረጃ ፫፡- ትንታኔ (Analysis)

የትንታኔ አሰራር፡-

a) ጽንሰ ሃሳቦችን ለማውጣት እንዲረዳ (Tool Used: Human-centered design, affinity clustering) [አባሪ 7]
    a. ከአዋቂዎች እና ከሕፃናት/ወጣቶች የተሰበሰቡት ድምጾች እያንዳንዱን ሃሳብ በመውሰድ
    b. ተመሳሳይ ሃሳቦችን በአንድ ምድብ በመመደብ
    c. ለምድቡ የሚሆን ማጠቃለያ በመስጠት
    d. ውይይቶችን በማበረታታት ጉዳዩን በበለጠ መረዳት
b) ለምናያቸው ውጤቶች ዋነኛ ምክንያቶች ምን እንደሆኑ ለመረዳት (Tool Used: Cause and Effect Ishikawa/Fishbone Diagraming) [ወጤት አባሪ 8]
    a. ደረጃ ሁለት ላይ የተዘረዘሩትን የጥናቱ 3 ትኩረቶች (Figure 2 ይመልከቱ) እንደ መሻሻያ እደል በማየት ለነዚህ ክፍተቶች የዳረጉትን ምክንያቶች በማጥናት
    b. በ6 ክፍሎች ምክንያቶቹ ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ በማጥናት (ክፍሎቹ፡- የሰው ሃይል/People, ሂደት/Process, አወቃቀር/Organization, መለኪያ/Measurement, የድጋፍ ምንጭ/Resource, and ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ያሉ ሁኔታዎች/ External Environment ናቸው)
    c. ለምክንያቶቹ ሌሎች ምክንያቶች ካሉ በመዘርዘር
    d. ውይይቶችን በማበረታታት ጉዳዩን በበለጠ መረዳት
c) ልጅ ተወልዶ ጠንካራ እስረካቢ አካል እንዲሆን በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ እንዲሄድበት የሚጠበቀው ሂደት (Tools used: Process flow/mapping) [አባሪ 9]
d) ጥንካሬያችንን፣ ድክመታችንን፣ እድሎቻችንን፣ እና ስጋታችንን ለመረዳት (Tool Used: Strength, Weakness, Opportunity, and Threat (SWOT) analysis) [አባሪ 10]
    a. በአራቱም ክፍሎች ያሉትን ጉዳዮች ዘርዝሮ በማውጣት
    b. እድሎቻችንን በማሰብ ለተዘረዘሩት ድክመቶች/የማደጊያ እድሎች ሊረዱ የሚችሉ የመፍትሄ ሃሳቦችን በማመንጨት

በትንታኔዎች ላይ ልጆችን ተረካቢ ትውልድ የሚያደርገው የቤተ ክርስቲያናችን (ከታች ይመልከቱ) በትክክሉ መረዳት ለውይይቶ እና ለሚቀረጹት መፍትሄዎች ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡ በተለይ ከአንድ አካል ወደ አንድ አካል ያሉ መስመሮችን የኃላፊነት ሽግግር እና እብሮ መስራትን ስለሚያሳዩ እንዲሁም በልጆች ክርስቲያናዊ እድገት ላይ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ያሉ ክፍሎች የተናበበ ስራ መስራት

በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኲሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሚቀጥለውን የእድገት እርምጃ ለመራመድ የሚያስችሏት ካህናት፣ ምዕመናን፣ እና ብዛት ያላቸው ተረካቢ ልጆች እግዚአብሔር ስላደላት፤ የጥናቱ አላማና ውጤትም ይህንን ለማስቻል እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ እንዳይውል ኮሚቴው አበክሮ ያሳስባል።

ምንኛ አስፈላጊ እንደሆነ ይጠቁማል፡፡ በተጨማሪም ልጆች በዋናነት በሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ ማደግ በዋናነት ሊሰመርበት እና በምዕመናኑም ዘንድ ያለው ግንዛቤ ዳብሮ እንዲሄድ፤ ብሎም ሰንበት ትምህርት ቤቱ ልጆቹን ሁሉ የሰንበት ተማሪ ለማድረግ የሚያበቃ አሰራር መቅረጹ ተገቢ ይሆናል፡፡ ኮሚቴው መፍትሄ ሲያቀርብ ይህንን ሂደት የበለጠ በማጠናከር እንጻር ይረዳሉ ያላቸውን መርሃ ግብሮች እና አሰራሮች ላይ በማተኮር ነው፡፡





*Figure 3 ልጆች በደብራችን አስረካቢ አካል እንዲሆኑ የሚሄዱበት ሂደት*

በሚከተሉት ክፍሎች ከተሰበሰቡት ድምጾች ላይ በመመርኮዝ ኮሚቴው መፍትሄ ይሆናሉ ያላቸውን ሃሳቦች ያቀርባል።

በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኩሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሚቀጥለውን የእድገት እርምጃ ለመራመድ የሚያስችሏት ካህናት፣ ምዕመናን፣ እና ብዛት ያላቸው ተረካቢ ልጆች እግዚአብሔር ስላደላት፤ የጥናቱ አላማና ውጤትም ይህንን ለማስቻል እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ እንዳይውል ኮሚቴው አበክሮ ያሳስባል።

## 7. ደረጃ ፬:- መፍትሄ (Recommendation )

እግዚአብሔር በልዩ በረከት ባርኮን፣ ቤተ ክርስቲያናችንን እስፍቶልን በይበልጥ ደግሞ ከ600 በላይ የሚሆኑ እድሜያቸው ከ 18 ያነሱ ተረካቢዎችን ስለሰጠን ዘወትር ስሞ ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ ክብር ምስጋና ይጋባው።

እግዚአብሔር የሰጠንን የልጆች በረከት ይዘን ወደሚቀጥለው የእድገት ደረጃ ያደርሱናል ያላቸውን የመፍትሄ ሃሳቦች ለማቅረብ ኮሚቴው የሚከተሉትን ዋና ዋና መርሆች ተጠቅሟል:-

a) የተረካቢ ትውልድ ማፍራት ጉዳይ ቤተ ክርስቲያኒቱ በልማት ለማደግ እያደረገች ካለችው የቤተ ክርስቲያን እና የመማሪያ ክፍሎች ሥራ ጋር በሰፊው የሚደጋገፍ ጉዳይ በመሆኑ፤ በተጓዳኝ ሊሰራና ተመሳሳይ priority ሊሰጠው እንደሚገባ

b) ወላጆች ልጆችን ተረካቢ በማድረግ በኩል የአንበሳውን ድርሻ ቢወስዱም ቤተ ክርስቲያን ደግሞ

    a. ልጆችን ዝግጁ ተረካቢ እንዲሆኑ የማድረግና

    b. ወላጆችን ጥሩ አስረካቢ አካል እንዲሆኑ የማስቻል ኃላፊነትን ልትይዝና ልትወጣ እንደሚገባ

c) ጠንካራ ተረካቢ ትውልድ ለማፍራት ብዙ የሚያያዙ ጉዳዮች ስላሉት የአንድ አካል ስራ ብቻ ሊሆን እንደማይገባ በረዳት ሁሉም አካላት ኃላፊነትን በመከፋፈል፤ ባለቤትነት (ownership) እና ተጠያቂነት ያለው (accountability) አሰራር ከማያቋርጥ ክትትል ጋር መዘርጋት እንዳለበት [አባሪ 11]

d) ሰዎች ላይ ሳይሆን ተቋማዊ አሰራር (system) ላይ ያተኮረ አሰራር መዘርጋት እንደሚገባ

e) ለልጆች እና ለልጆች ጉዳይ ቦታ እና ቅድሚያ የሚሰጥ፤ ልጆች ወደ እግዚአብሔር ቤት ሲመጡ ሁሉም በፍቅር ሊቀበላቸው፣ መታረም የሚገባቸውን ጉዳዮች በፍቅር ሊያስተምራቸው፣ ከውጪ ያላባቸውን ጫና ሊረዳላቸው፣ እና በቋንቋ ምክናያት የሚገጥማቸውን ክፍተት የሚቀርፍላቸው የሚገባ አቀራረብ እንዲፈጠር (cultural and mindset shift)፤ በመጨረሻም

f) ልጆችና ወጣቶች ለራሳቸውም ሆነ ለቤተ ክርስትያናቸው ብዙ ድጋፍ ሊያደርጉ ስለሚችሉ የራሳቸውን እድሜ ክልል ሊያገለግሉ በሚችሉበት መልኩ መሪዎች እንዲሆኑ ማስቻል እንደሚገባ በማመን ወደ አንኩዋር የሆኑ መፍትሄ ሃሳቦች ላይ አተኩሯል።

አወደ ጥናቱ በዋናነት ዘላቂ መፍትሄ ለማግኘት ይረዳል ብሎ ከደረጃ ፩ እስከ ደረጃ ፫ በነበሩት ጥናቶች ላይ በመደገፍ፣ ቃለ ዓዋዲ እና የቤተ ክርስቲያኒቱን ህግ እና ደንብ በመመርመምር፣ ለቤተ ክርስቲያኑ ሰበካ ጉባኤ የሚከተሉትን የመፍትሄ ሰነዶች አቅርቧል:-

a) በሚቀጥለው አንድ ዓመት ውስጥ ሊሰራባቸው ይገባቸውል ያላቸውን አዳዲስ እና መጠናከር ያለባቸው መርሃ ግብሮች

b) መፍትሄዎችን ዘላቂ ሊደግፍ የሚችል የሰበካ ጉባኤ መዋቅር፤ በአንድ ዓመት ውስጥ ወደ ተግባር የሚሄድ

c) በሚቀጥለው አንድ ዓመት ውስጥ በጀት ተይዘው ሊሰራባቸው ይገባቸውል ያላቸውን

በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኩሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሚቀጥለውን የእድገት እርምጃ ለመራመድ የሚያስችሏት ካህናት፣ ምዕመናን፣ እና ብዛት ያላቸው ተረካቢ ልጆች እግዚአብሔር ስላደላት፤ የጥናቱ አላማና ውጤትም ይህንን ለማስቻል እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ እንዳይውል ኮሚቴው አበክሮ ያሳስባል።

d) ለእቅዱ ማስፈጸሚያ ገንዘብ ከየት ሊገኝ እንደሚችል እና ይህ በጀት ከ 10 እስከ 15 ዓመት ውስጥ የሚሰጠው የገንዘብ ጥቅም (return on investment/Net Present Value)

e) በመፍትሄ ሃሳቦች ላይ የተመረኮዘ የ5 ዓመት ስልታዊ እቅድ እንዲሁም

f) ለወደፊት ሊታሰብባቸው የሚገባቸው ልዩ ልዩ የመፍትሄ ሃሳቦች [አባሪ 12]

ከ a እስከ e ያሉት በዚህ ክፍል ውስጥ ተካተዋል።

**a) በ2022/2023 የእቅድ አመት ውስጥ ሊሰሩ የሚገባቸው አዳዲስ እና መጠናከር ያለባቸው መርሃ ግብሮች**

ቤተ ክርስቲያናችን የእድገት ደረጃዋን ጠብቃ ወደፊት ስትራመድ አገልግሎት ለማስፋትም ሆነ ክፍተቶችን ለመሙላት በተለያየ ወቅት ብዙ አዳዲስ ነገሮች ሲሞከሩ ይታያል። አንዳንድ ሙከራዎች እጅግ ብዙ ጠቃሚ ውጤት የሚያሳዩ ቢሆንም በሰዎች አነሳሽነት ብቻ የሚጀመሩ ሆነው እና በቤተ ክርስቲያኑ መዋቅር ውስጥ ሳይያዙ ሲቀር ዘለቄታነት ሳይኖራቸው ይቀራሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ሃላፊነት ያላቸው ቦታዎች በፈቃደኛ ምዕመናን ካልተደገፉ ለአገልግሎት ጫና በጣም ይጋለጣሉ። ይህም የሚፈለገውንና የሚጠበቀውን አገልግሎት ለማሟላት ብሎም የእድገት ደረጃን ጠብቆ ለመሄድ አዳጋች ያደርገዋል። ከዚህም ባሻገር ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን የሚያካትቱ አገልግሎቶች የሁሉንም እርዳታ በሚያካትትና ግልጽ ተጠያቂነት ባለው መልኩ አለመቀረጻቸው የተሳለጠ እና ለብዞዎች የሚደርስ ውጤት ያለው ሥራ እንዳያሳዩ እንቅፋት ሲሆን ይታያል።

በተረካቢ ትውልድ ዙሪያም ለሚሰሩ ሥራዎች እያደጉ ሲመጡ

i. የመዋቅር፣

ii. የሰው ሃይልና፣

iii. ሁሉን ሳትፎ ተጠያቂነት ያለው አሰራር ያለመኖር ክፍተቶች ተጽእኖ ፈጥሮባቸዋል።

በአጥር በተከለለ ስፍራ ላይ ወደፊት የሚጓዝ ሰው ሄዶ ሄዶ አጥሩ ጥግ መድረሱ እንደማይቀር ሁሉ፤ በሆነ ወቅት ላይ እድገት ቀድሞ ተዘርግተው ሲሰራባቸው የነበሩትን አሰራሮች እንዲፈትሹ የሚያደርግበት ጊዜ ያመጣል። ቤተ ክርስቲያኒቱ እየሰራችበት ያለችውንት ጠንካራ ተረካቢ ትውልድ የመቅረጽ አላማ ደረጃውን በጠበቀ መሰረት እንዲቀጥል እድገታችን ያሳየንን ክፍተቶች መሙላት ተገቢ ይሆናል።

በአወደ ጥናቱ መሰረት ኮሚቴው ጠንካራ ተረካቢ ትውልድ ለመቅረጽ ቤተ ክርስቲያኒቱን ወደፊት የሚያራምዳት 4 መርሃ ግብሮች እንዲቀረጹ የመፍትሄ ሃሳብ ይሰጣል። እነኝህም፡-

i. የትምህርት መርሃ ግብር (Education Program) -- የሚያካትተው

a. የአብነት ትምህርት ቤት

በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኩሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሚቀጥለውን የእድገት እርምጃ ለመራመድ የሚያስችሏት ካህናት፣ ምዕመናን፣ እና ብዛት ያላቸው ተረካቢ ልጆች እግዚአብሔር ስላደላት፤ የጥናቱ አላማና ውጤትም ይህንን ለማስቻል እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ እንዳይውል ኮሚቴው አበክሮ ያሳስባል።

b. ሥርዓተ ትምህርት (Curriculum) -- መስራት፣ ማሰራት፣ ማደስ [መጀመሪያ በእንግሊዘኛ ለሁሉም ክፍሎች፤ በመቀጠል በአማርኛ በተለይ ወላጅ እንዲያግዝ እንዲረዳ]
c. አስተማሪ ማፍራት / ማሰልጠን

ii. የህፃናት እና የወጣቶች ተልእኮ (Youth Development Program) -- ለወደፊቱ ከውጪ እርዳታ (grant) የሚገኝበትን ሁኔታ ለማመቻቸት እንዲረዳ ሆኖ የተቀረጸ ሲሆን የሚያካትተው

a. የህፃናት እና የወጣቶች ዝግጅት (በተለይ 18+ የሆኑትን ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚያቀርቡ)
b. የህፃናት እና የወጣቶች ጤና (በተለይ ከማኅበረ ካህናት እና ከጤና ክፍል ጋር አብሮ በመስራት የልጆችን የአእምሮ ጤና መጠበቅ)
c. የትምህርት እና የእድገት መርሃ ግብር (Professional Programing)
d. የህፃናት እና የወጣት መሪዎች ማፍሪያ (Experiential Leadership Training/Train the trainers)
e. የአዘቦት ቀን የሃይማኖት ትምህርት (ለምሳሌ አርብ ማታ) በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ አሁን አርብ የሚሰጥ የሰርክ ጉባኤ ስላለ ያንን ቀን መጠቀሙ ወላጆችም ወደ ጉባኤው በመሄድ ትምህርት ሊቀስሙ ስለሚችሉ አርብን በምሳሌነት ተጠቁሟል። ይህ የአዘቦት ቀን ትምህርት ልጆች በእሑድ እለት በሰንበት ትምህርት ቤት የሚማሩትን የሃይማኖት ትምህርት የበለጠ የሚያጠናክር፣ ልጆች የቅዳሴ ተሰጥዎ የሚማሩበት እና ሥርዓተ ትምህርቱን የሚደግፉ ብሎም ማኅበራዊ ግንኙነት የሚያጠናክሩ እንቅስቃሴዎች (age-appropriate activities) የሚያደርጉበት ይሆናል። በተጨማሪም ልጆች በሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ እንዲያድጉ የሚበረታቱበት መንገድን ከሰንበት ትምህርት ቤቱ ጋር ይሰራል፡፡

iii. የወላጆች/የቤተሰብ መርሃ ግብር (Parent/Family Program) -- ለወደፊቱ ከውጪ እርዳታ (grant) የሚገኝበትን ሁኔታ ለማመቻቸት እንዲረዳ ሆኖ የተቀረጸ ሲሆን የሚያካትተው

a. የወላጆች ትምህርት (Parent Education)
b. የምክር አገልግሎት (Counseling)
c. የመደጋገፊያ ማኅበር (Support groups)

iv. የእንግሊዘኛ አገልግሎት (English Service) -- የሚያካትተው

a. የሃይማኖት ትምህርት (Courses in English)
b. ጉባኤ ከ18 በላይ ለሆኑ (Monthly Spiritual Assembly)
c. እንግሊዘኛ በቅዳሴ ላይ (15 ደቂቃ ትምህርት እና ንባባት)
d. ማካተት (Communication/announcements/etc)

በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኩሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሚቀጥለውን የእድገት እርምጃ ለመራመድ የሚያስችሏት ካህናት፣ ምዕመናን፣ እና ብዛት ያላቸው ተረካቢ ልጆች እግዚአብሔር ስላደላት፤ የጥናቱ አላማና ውጤትም ይህንን ለማስቻል እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ እንዳይውል ኮሚቴው አበክሮ ያሳስባል።

### b) መፍትሄዎችን ዘላቂ ሊደግፍ የሚችል የሰበካ ጉባኤ መዋቅር

ከላይ የተዘረዘሩትን መርሃ ግብሮች አሳልጦ ለማካሄድ የሚከተለውን የመዋቅር ለውጥ እንዲደረግ ኮሚቴው በአንክሮ ይመክራል። ይህም በ6 ወር ተጠንቶ በአጋማሽ አመቱ ላይ ለአጠቃላይ ጉባኤው ቀርቦ ቢጸድቅ አስመራጭ ኮሚቴው ሲመረጥ ተጨማሪውን የሰበካ ጉባኤ አባል ለሚቀጥለው ሰበካ ጉባኤ ማስመረጥ ይችላል። ስለዚህ ሰበካ ጉባኤው ይህንን የጊዜ ሰሌዳ በአንክሮ እንዲመለከተው ኮሚቴው ይጠይቃል።





*Figure 4 ተረካቢ ትውልድን ለማፍራት የሚረዳ መዋቅራዊ ለውጥ*

### c) በሚቀጥለው አንድ ዓመት ውስጥ በጀት ተይዘው ሊሰራባቸው የሚገባ

በ4ቱ መርሃ ግብሮች ውስጥ የተካተቱት ንዑስ መርሃ ግብሮች በተሳካ መልኩ እንዲፈጸሙ ለማድረግ ባለቤትነት እና ተጠያቂነት ያለው አሰራር መዘርጋት ተገቢ ይሆናል። ለዚህም እንዲረዳ የሚከተለውን ኮሚቴው መፍሄ ያቀርባል (Tool Used: Responsibility Assignment Matrix, aka RACI/DRASCI

i. ሚና/ Role -- -- ይህ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ያለ አካል የሚጫወተውን ሚና ያሳያል

በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኵሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሚቀጥለውን የእድገት እርምጃ ለመራመድ የሚያስችሏት ካህናት፣ ምዕመናን፣ እና ብዛት ያላቸው ተረካቢ ልጆች እግዚአብሔር ስላደላት፣ የጥናቱ አላማና ውጤትም ይህንን ለማስቻል እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ እንዳይውል ኮሚቴው አበክሮ ያሳስባል።

| ROLES | Church Administrator | Education and Youth Dev Dept. Head | Evangelism Dept. Head | Sunday School Hitsanat Kifil | Sunday School Timihirt Kifil | Youth Dev. Program (Coordinator(s)) | Deacon/Teacher English | Parent Committee | Teachers | Education Program | Volunteers / Parishioners | Clergy Council | Parish Council | Faith Community Health Program | Internal Audit | PC Public Relations |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|

*Figure 5 ሚና*

ii. ኃላፊነት/Responsibilities -- ይህ እያንዳንዱ ተሳታፊ በመርሃ ግብሩ ላይ የሚወስደውን ኃላፊነት ያሳያል

| | | |
|---|---|---|
| D | Driver | Assists those who are responsible for a task. |
| R | Responsible | Assigned to complete the task or deliverable. |
| A | Accountable | Has final decision-making authority and accountability for completion. Only 1 per task. |
| S | Support | Provides support during implementation. |
| C | Consulted | An adviser, stakeholder, or subject matter expert who is consulted before a decision or action. |
| I | Informed | Must be informed after a decision or action. |

*Figure 6 ኃላፊነት*

iii. ሚና እና ኃላፊነት (Roles and responsibilities) -- ይህ ቀድሞ የተዘረዘሩት 4ቱ መርሃ ግብሮች በመግለጽ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ አካላት ያላቸውን ኃላፊነት ያሳያል

በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኩሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሚቀጥለውን የእድገት እርምጃ ለመራመድ የሚያስችሏት ካህናት፣ ምዕመናን፣ እና ብዛት ያላቸው ተረካቢ ልጆች እግዚአብሔር ስላደላት፤ የጥናቱ አላማና ውጤትም ይህንን ለማስቻል እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ እንዳይውል ኮሚቴው አበክሮ ያሳስባል።

| Deliverable or Task | Status | Church Administrator | Education Dept. Head | Evangelism Dept. Head | Sunday School Hitsanat Kifil | Sunday School Timihirt Kifil | Youth Dev. Program (Coordinator(s)) | Deacon/Teacher English | Parent Committee | Teachers | Education Program | Volunteers / Parishioners | Clergy Council | Parish Council | Faith Community Health Program | Internal Audit | PC Public Relations |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ROLES | | Sponsor / Leadership | | | | | Project Team | | | | | | Other Resources | | | | |
| **Education Program** | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| Abinet Timihirt | | | A | | C | | | | | | R | | S | I | | I | |
| Curriculum (Sunday/Friday) | | | A | C | R | R | I | | | S | R | | | D | | I | |
| Teacher Curriculum Certification | | | A | C | C | R | | | | S | R | | | D | | I | |
| **Youth Development Program** | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| Youth Program | | | A | C | D | D | R | S | | | | S | | I | | I | |
| Youth Health | | | A | C | C | | R | | | | | | | I | S | I | |
| Professional Programming (TA-ARC) | | | A | | C | D | R | | C | | | S | | I | | I | |
| Leadership Training (Experential) | | | A | | D | S | R | | | C | | | | I | | I | |
| Weekday Faith Education (e.g. Friday) | | | A | | S | D | R | R | | R | | R | | I | | I | |
| **Parent/Family Program** | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| Parent Education | | | I | A | C | S | | | R | | | S | | I | | I | |
| Parent Counseling (1:1) | | | C | A | | | | | R | | | | R | I | R | I | |
| Support Groups | | | C | A | | | | | R | | | | | I | | I | |
| **English Service** | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| Courses in English | | | C | A | R | C | S | R | | S | | | | I | | I | |
| English Gubae | | | C | A | S | S | | R | | | | | R | I | | I | |
| English Qidase | | | | A | I | I | S | R | | | | | R | D | | I | |
| Communication (e.g. announcement) | | | | C | | | | R | | | | | | D | | I | A |

*Figure 7 ተረካቢ ትውልድ ለማፍራት የሚረዱ መርሃ ግብሮች እና የተለያዩ ክፍሎች የሚይዙት ኃላፊነት*

ከላይ የተጠቀሱትን መርሃ ግብሮች ለማሳካት በ 2022/2023 በጀት ዓመት የሚከተሉት በእቅድ ተይዘው፤ ሰበካ ጉባኤው ለአጠቃላይ ጉባኤው በማቅረብ እንዲያጸድቅ ኮሚቴው ሃሳቡን ይሰጣል።

በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኩሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሚቀጥለውን የእድገት እርምጃ ለመራመድ የሚያስችሏት ካህናት፣ ምዕመናን፣ እና ብዛት ያላቸው ተረካቢ ልጆች እግዚአብሔር ስላደላት፤ የጥናቱ አላማና ውጤትም ይህንን ለማስቻል እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ እንዳይውል ኮሚቴው አበክሮ ያሳስባል።

ለመጀመሪያ ዓመት እቅድ ውስጥ እንዲገባ የተጠየቀ በጀት

(ለሰበካ ጉባኤው የገባ)

*Figure 8 ለመጀመሪያ ዓመት እቅድ ውስጥ እንዲገባ የተጠየቀ በጀት*

በተለይ ተቀጣሪ የሆኑትን አካላት (Volunteer Coordinator(s) and Teacher/Deacon for English Service) የሚያገለግሉዋቸውን ልጆች በደንብ ሊረዱ የሚገቡ፣ በእድሜ ከወጣቶቹ ብዙ እርቀት የሌላቸው፣ ተረካቢ ትውልድ ለማፍራት ሙሉ ፍላጎት ያላቸው (ቢቻል ከዚህ ቀደም በልጆች ዙሪያ የበኩላቸውን አስተዋጽዎ ያደረጉ ቢሆኑ እና ለ Volunteer Coordinators ቢቻል አንድ ሴት እና አንድ ወንድ ቢቀጠሩ፤ እንዲሁም ለTeacher/Deacon for English Service ቢቻል ዲያቆን አለዚያም በቤተ ክርስቲያን ትምህርት እወቀቱ ያለው ቢሆን ይመረጣል።

በተጨማሪም ሰበካ ጉባኤው በአቀጣጠሩ ላይም ሆነ በግምገማው ላይ ከተለያዩ አካላት የተውጣጣ ኮሚቴ የውሳኔ ሃሳቦችን እና አስተያየቶችን እንዲሰጥ ማካተቱ ጠቃሚ ይሆናል።

የሰበካ ጉባኤው አወቃቀር ከ6 - 12 ወር ውስጥ እስኪቀየር ድረስ፤ ባጀቱ እና 4ቱ መርሃ ግብሮች ይህ ዘገባ በሚጻፍበት ወቅት ተጣምሮ ባለው አወቃቀር መሰረት በስብከተ ወንጌል እና ትምህርት ክፍል ውስጥ እንዲቋቋሙ ኮሚቴው ይመክራል።

በመጨረሻም በመጪው አንድ አመት ውስጥ የሚሰሩትን ከላይ የተዘረዘሩትን የተረካቢ ትውልድ ስራዎች የሚከታተል እና ለሰበካ ጉባኤው ተጠሪ የሆነ ኮሚቴ እንዲያዋቀር እና እቅዶች ያለምንም እንቅፋት በቶሎ ወደ ሥራ እንዲተረጎሙ እንዲያደርግ ኮሚቴው ይመክራል።

በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኲሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሚቀጥለውን የእድገት እርምጃ ለመራመድ የሚያስችሏት ካህናት፣ ምዕመናን፣ እና ብዛት ያላቸው ተረካቢ ልጆች እግዚአብሔር ስላደላት፤ የጥናቱ አላማና ውጤትም ይህንን ለማስቻል እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ እንዳይውል ኮሚቴው አበክሮ ያሳስባል።

**d) ለእቅዱ ማስፈጸሚያ ገንዘብ ከየት ሊገኝ እንደሚችል እና ይህ በጀት ከ 10 እስከ 15 ዓመት ውስጥ ሊያመጣ የሚችለው የገንዘብ ጥቅም (return on investment/Net Present Value)**

ከላይ በአንድ አመት እንዲሰሩ የተዘረዘሩትን የመፍትሄ ሃሳቦች ለማሳካት ቤተ ክርስቲያኒቱ የተለያዩ የገንዘብ ማግኛ ምንጮችን ልትጠቀም ትችላለች። ለምሳሌ በሚቀጥለው ሰንጠረዥ/Table እንደሚታየው ከተለያዩ ገቢዎች የተወሰኑትን በመምረጥ ሰበካ ጉባኤው የታቀደውን ሊያሟላ ይችላል። ለምሳሌ፡- እማራጭ 1 / option 1 እንደሚያሳየው ኮሚቴው ምዕመናን የተረካቢ ትውልድን ጉዳይ አንድ እርምጃ ወደፊት ለማስኬድ እርዳታ ቢጠየቅ በአንድ ቀን እስከ $40ሺ ሊያስገባ ይችላል። በተጨማሪም ቤተ ክርስቲያኒቱ ቅዳሜ በምትሰጠው ትምህርት በአማካይ 300 ተማሪዎች በሴሚስተር $20ብር ከፍለው ቢመዘገቡ በአመት $12ሺ ማኘት ይቻላል። በተጨማሪም ቤተ ክርስቲያኑ ከጉዳዩ አንገብጋቢነት በመነሳት እና ለተረካቢ ትውልድ $25ሺ ቢመድብ በአጠቃላይ $77ሺ በማግኘት በጀቱን ሊሸፍን ይችላል። ከዚህ ባሻገር ሌሎች ሶስት አማራጮች የተቀመጡ ሲሆን ሰበካ ጉባኤ እና አጠቃላይ ጉባኤው ከዚህም የተሻሉ መንገዶችን ሊዘረጋ ይችላል። ወደፊት ደግሞ በተለይ በYouth Development Program እና በParent Program ሥር በተለይ ጤናን፣ የቤተሰብ እንክብካቤን፣ የወላጅ ድጋፍ ለመስጠት ከተለያዩ የመንግስት ተቋማት የሚወጡ የገንዘብ እርዳታዎችን / grants (ከቤተ ክርስቲያናችን አመለካከት የማይጣረሱትን) በመከታተል ለልጆችና ለወላጆች ተጨማሪ አገልግሎት መስጠት ይቻላል። እነኝህን መርሃ ግብሮች በገንዘብ ከመደገፍ ባሻገር ተፈጻሚነታቸውን በመከታተል ሰበካ ጉባኤው ተረካቢ ትውልድ ላይ ትልቅ ሥራ እንዲሰራ እና ከርእሰ አድባራት አልፎ ለሌሎችም አድባራት ፈር ቀዳጅ ሥራን ሊያሳይ ይችላል።

## መርሃ ግብሮችን ለማከናወን እንዲረዳ ገንዘብ የማሰባሰቢያ አማራጮች
(ለሰበካ ጉባኤው የገባ)

*Figure 9 መርሃ ግብሮችን ለማከናወን እንዲረዳ ገንዘብ የማሰባሰቢያ አማራጮች*

ከሂሳባዊ ስልት አንጻርም ሲታይ፤ በሚቀጥሉት አመታት ለነዚህ መርሃ ግብሮች በበጀት የሚያዘው ገንዘብ ከሚያመጣው የገንዘብ ስሌት ሲሰላ በሁለት አመት ውስጥ ዋጋውን የሚመልስ ብሎም በአስር ዓመት ውስጥ ከ$100ሺ ብር በላይ ሊያስገኝ ይቻላል (የሚቀጥለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ)። ከገንዘቡ ባሻገር በህብረት የሚሰሩት ስራዎች ዋናውን አላማ ልጆችን የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ጠንካራ ተረካቢ እንዲሆኑ ያስችላቸዋ።

## አሁን የሚወጣው ገንዘብ ወደፊት ሊያስከትል የሚችለው የገቢ መጠን
(ለሰበካ ጉባኤው የገባ)

*Figure 10 አሁን የሚወጣው ገንዘብ ወደፊት ሊያስከትል የሚችለው የገቢ መጠን*

በየአመቱ ከቤተ ክርስቲያኑ የሚመረቁ ወጣቶችን ቤተ ክርስቲያኒቱ ክትትል ልታደርግላቸው ይገባል። በተለይም የሁለተኛ ደረጃ ተመራቂዎች 18ሲሞላቸው የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት እንዲሆኑ ሰበካ ጉባኤው ቢያመቻች እና የንስሐ አባት እንዲይዙ ቢያደርግ ለክትትል የበለጠ ምቹ ይሆናል።

### e) በመፍትሄ ሃሳቦች ላይ የተመረኮዘ የ5 ዓመት ስልታዊ እቅድ

እግዜብሔር ቢፈቅድ በመጀመሪያ የእቅድ ዓመት (July 1, 2022 – June 30, 2023) ተሰርተውና አስፈላጊው ግምገማ ከተደረገ በኋላ ሰበካ ጉባኤው የሚቀጥለውን ዓመት በጀት መርሃ ግብሮቹን በግምገማው መሰረት ሊያስቀጥሉ የሚችል በጀት እንዲያወጣ እና

በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኩሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሚቀጥለውን የእድገት እርምጃ ለመራመድ የሚያስችሏት ካህናት፣ ምዕመናን፣ እና ብዛት ያላቸው ተረካቢ ልጆች እግዚአብሔር ስላደላት፤ የጥናቱ አላማና ውጤትም ይህንን ለማስቻል እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ እንዳይውል ኮሚቴው አበክሮ ያሳስባል።

ለሚቀጥለው ሰበካ ጉባኤ አስፈላጊውን እገዛ በማድረግ ለታሰበለት አላማ መሳካት ትልቅ ሚና እንዲጫወት ኮሚቴው ከታላቅ አደራ ጭምር ያሳስባል።




*Figure 11 የአምስት አመት ስልታዊ እቅድ (ጠንካራ ተረካቢ ትውልድ ለማፍራት)*

ይህ የአምስት ዓመት ስልታዊ እቅድ በቤተ ክርስቲያኒቱ እቅድ እና ልማት ሥር ሆኖ በየአመቱ February – April እየተመረመረ፣ እየተሻሻለ፣ እና በሰበካ ጉባኤው እየጸደቀ ለስራ እንዲውል ቢደረግ ለአሰራር ቀጣይነት ጥሩ ሚና ይጫወታል።

አያይዞም በየአመቱ ከሚቀጥለው የበጀት አመት በፊት ሰበካ ጉባኤው መለኪያ Metric የወጣላቸውን መርሃ ግብሮች በመገምገም የታለመለትን ደረጃ መድረሱን እንዲከታተል፤ መስተካከል ያለባቸውን የወደፊት እቅዶች እንዲይስተካከል፤ ብሎም ግባቸውን ያልመቱትን ምክኒያታቸውን አጥንቶ አስፈላጊውን ውሳኔ እንዲወስድ፤ ይህም አሰራር ዘወትር Mayውስጥ ከሚደረገው የእቅድ እና በጀት አወጣጥ ሂደት ውስጥ እንዲካተት ኮሚቴው ይመክራል።

ለዚህ አወደ ጥናት ትልቅ ግብአት ሆነው የተገኘው ከወጣቶች ጋር የተደረጉ ውይይቶችን (workshops) እና  ከልጆች የተሰበሰቡት መጠይቆችን መነሻ በማድረግ፤ ሰበካ ጉባኤው በየአመቱ ተመሳሳይ መጠይቆችን በማድረግ መርሃ ግብሮቹ በልጆች ላይ እያመጡ ያሉትን ማሻሻያዎች ቢገመግም ለታቀደው አላማ ጥሩ ሂደትን ይፈጥራል።

በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኩሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሚቀጥለውን የእድገት እርምጃ ለመራመድ የሚያስችሏት ካህናት፣ ምዕመናን፣ እና ብዛት ያላቸው ተረካቢ ልጆች እግዚአብሔር ስላደላት፤ የጥናቱ አላማና ውጤትም ይህንን ለማስቻል እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ እንዳይውል ኮሚቴው አበክሮ ያሳስባል።

በመጨረሻም የታቀዱት ስራዎች ብዙ ቢመስሉም ከእግዚአብሔር ጋር ቤተ ክርስቲያኒቱ መጠነ ሰፊ የሰው ሃብት ስላላት በተለይ በሚቀጥለው የሚጣዩት ስድስት አካላት ህብረት በመስራት ጠንካራ ተረካቢ ትውልድን በቀላሉ እንደምታፈራ ኮሚቴው ባለሙሉ ተስፋ ነው፡፡




*Figure 12ጠንካራ ተረካቢ ለማፍራት የሚቻለው በመተባበር ብቻ ነው*

በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኩሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሚቀጥለውን የእድገት እርምጃ ለመራመድ የሚያስችሏት ካህናት፣ ምዕመናን፣ እና ብዛት ያላቸው ተረካቢ ልጆች እግዚአብሔር ስላደላት፤ የጥናቱ አላማና ውጤትም ይህንን ለማስቻል እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ እንዳይውል ኮሚቴው አበክሮ ያሳስባል።

## 8. ማጠቃለያ





*Figure 13 ከአማስት አመት በኋላ የሚጠበቁ ለውጦች*

1. ጠንካራ ተረካቢ ትውልድ ለማፍራት በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኲሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን **<u>እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው።</u>**
2. እግዚአብሔር ተረካቢ ትውልድ በሚሆኑ ብዙ ልጆች ባርኮናል።
3. እግዚአብሔር የሰጠንን **<u>አንድ ልጅ ሳይቀር ሁሉንም ልጆች</u>** የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ተረካቢ እንዲሆኑ ማስቻል የማኅበረ ካህናት፣ የሰንበት ትምህርት ቤት፣ የወላጆች፣ የሰበካ ጉባኤ፣ የሰብከተ ወንጌል እና የትምህርት ክፍል ግዴታ ነው።
4. ወላጆችን ዋነኛውን ሚና እንዲጫወቱ፣ የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ ማድረግ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ አካላት ሁሉ ሊረባረቡበት ይገባል። **<u>ድርሻቸውን ለመወጣት ወላጆች እርዳታ ይሻሉ፤</u>** ቤተ ክርስቲያኒቱም ይህንን ተገንዝባ ከጎናቸው ልትቆም ይገባል።
5. ልጆችን ከ3 ዓመት ጀምሮ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማሳደግ ከስርዓተ ትምህርት ጀምሮ በቂ አስተማሪዎችን ማፍራት፣ እንዲሁም ልጆቹን ማእከላዊ ባደረገ የትምህርት አሰጣጥ (including well planned and intentional activities and social time) የልጆችን ትምህርት ወጤታማ እንዲሆን ማድረግ ይገባል። እነዚህን ለማሳካት በተራ ቁጥር ሶስት የተዘረዘሩት አካላት በህብረት የተናበበ ሥራ እንዲሰሩ ሰበካ ጉባኤው ትልቅ ኃላፊነት መወሰድ ይኖርበታል።
6. ልጆች በሚገባቸው ቋንቋ በተለይ በእንግሊዘኛ ሃይማኖታቸውን፣ ወንጌልን፣ የቤተ ክርስቲያናቸውን ቀኖና፣ ዶግማ እና ስርዓት እንዲያውቁ ማድረግ የቤተ ክርስቲያኒቱ ተቀዳሚ ተግባሯ ሊሆን ይገባል።
7. በጽኑ መሰረት ላይ የተቀረጹትን ልጆች 18 ከሞላቸውም በኋላ ቃለ እግዚአብሔርን እንዲሰሙ፣ የሚገጥማቸውን ጉዳይ (challenge) በመስማት እርስ በ እርስም ሆነ በካህናት፣ እንዲሁም በማለሙያዎች እንዲረዱ፣ ህይወታቸውን በአገልግሎት በመጥመድ ለሌሎች ብርሃን እንዲሆኑ ማስቻል የቤተ ክርስቲያኒቱ አላማ ሊሆን ይገባል።
8. እድገታችን በጠበቀ መልኩ ወደፊት መራመድ ክርስቲያናዊ ግዴታችን ነው።
9. ከጥፋት በተለይ ከሃይማኖታዊ ጥፋት ልጆችን መጠበቅ **<u>የዛሬ ስራ</u>** ነው።
10. ዛሬ የሚደከምላቸው ልጆች በሃማኖት ታንጸው፤ ነገ ራሳቸውን ከመጠበቅ አልፈው
    a. ወንድም እና እህቶቻቸውን የሚያስተምሩ፣
    b. ደብራቸውን በሙያ፣ በጉልበትና በገንዘብ የሚደግፉ፣
    c. ከደብር አልፈው ለታላቂቱ እናት ቤተ ክርስቲያን አለኝታ የሚሆኑ፣ ብሎም
    d. ለሃገር እና ለወገን የሚጠቅሙ

    ስለሚሆኑ፤ የዛሬው ድካም በነገው ተስፋ ሙሉ እንደሚሆን በማመን እጅ ለእጅ ተያያዞ፣ ተቀዳሚ ስራ በማድረግ፣ ሁሉም ዛሬ ተረካቢ ትውልድ ላይ በህብረት ሊሰራ ይገባል።

በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኲሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሚቀጥለውን የእድገት እርምጃ ለመራመድ የሚያስችሏት ካህናት፣ ምዕመናን፣ እና ብዛት ያላቸው ተረካቢ ልጆች እግዚአብሔር ስላደላት፤ የጥናቱ አላማና ውጤትም ይህንን ለማስቻል እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ እንዳይውል ኮሚቴው አበክሮ ያሳስባል።

## 9. አባሪ፡- የአውደ ጥናቱ አባላት ዝርዝር

- ካህናት፡-
  - መጋቢ ሃይማኖት ቀሲስ አሃዱ አስረስ
  - ዲ/ን ሙሴ አለማየሁ
- ሰንበት ትምህርት ቤት፡-
  - አቶ ለአአለም ጥበቡ (የቤዛ ኵሉ ሰንበት ት/ት ቤት ሰብሳቢ)
  - ወ/ት እግዚእኃርያ ይልማ
  - ወ/ሮ ሰፋኒት መልሴ
  - ወ/ት ሕሊና ታደሰ
- ሰበካ ጉባኤ፡-
  - ዶ/ር ዮሃንስ ታደሰ
  - ወ/ሮ ጺዮን መኮንን
  - ዶ/ር ኤልያስ አያና
- መምህራን፡-
  - አቶ የኔገኘሁ ገብረማርያም
  - ወ/ሮ ሂሩት ግሸን
  - አቶ አብርሃም ሰለሞን
- ወላጆች፡-
  - ወ/ሮ ደብሪቱ በለጠ
  - አቶ መስፍን መኮንን
  - ወ/ሮ እፀገነት ለማ
  - ወ/ሮ ማርታ ፈቃደ
  - አቶ ፀጋዬ ሺበሺ
  - ወ/ሮ ብሌን ሸዋቀና
- ወጣቶች፡-
  - ወ/ት ልዕልና ደስታ
  - ወ/ት ኔዮሚ ዮሴፍ

# ወስብሃት ለእግዚአብሔር

በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኵሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሚቀጥለውን የእድገት እርምጃ ለመራመድ የሚያስችሏት ካህናት፣ ምዕመናን፣ እና ብዛት ያላቸው ተረካቢ ልጆች እግዚአብሔር ስላደላት፤ የጥናቱ አላማና ውጤትም ይህንን ለማስቻል እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ እንዳይውል ኮሚቴው አበክሮ ያሳስባል።

## 10. ተጨማሪ አባሪዎች (አባሪ 1-12 )

በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኵሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሚቀጥለውን የእድገት እርምጃ ለመራመድ የሚያስችሏት ካህናት፣ ምዕመናን፣ እና ብዛት ያላቸው ተረካቢ ልጆች እግዚአብሔር ስላደላት፤ የጥናቱ አላማና ውጤትም ይህንን ለማስቻል እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ እንዳይውል ኮሚቴው አበክሮ ያሳስባል።

በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኲሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሚቀጥለውን የእድገት እርምጃ ለመራመድ የሚያስችሏት ካህናት፣ ምዕመናን፣ እና ብዛት ያላቸው ተረካቢ ልጆች እግዚአብሔር ስላደላት፤ የጥናቱ አላማና ውጤትም ይህንን ለማስቻል እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ እንዳይውል ኮሚቴው አበክሮ ያሳስባል።

በማኅበረ ካህናት፣ በቤዛ ኲሉ ሰንበት ት/ቤት፣ እና በመምህራን እየተደረገ ያለው ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሚቀጥለውን የእድገት እርምጃ ለመራመድ የሚያስችሏት ካህናት፣ ምዕመናን፣ እና ብዛት ያላቸው ተረካቢ ልጆች እግዚአብሔር ስላደላት፤ የጥናቱ አላማና ውጤትም ይህንን ለማስቻል እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዓላማ እንዳይውል ኮሚቴው አበክሮ ያሳስባል።